# የአሌክሳንድሪያ ከተማ የትምህርት ቤት ዞን የፍጥነት ካሜራዎች የሚተከሉባቸውን ቦታዎች ይፋ አደረገ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ በዚህ ዓመት በሚከተሉት የትምህርት ቤት ዞኖች ውስጥ የፍጥነት ካሜራዎችን ለመትከል አቅዷል፡-

- **ፍራንሲስ ሃሞንድ ሚድል ትምህርት ቤት** (ሴሚናሪ መንገድ፣ በኬንሞር ጎዳና እና በኖርዝ ጆርዳን መንገድ መካከል)
- **ጆን አዳምስ ኢለመንተሪ ትምህርት ቤት እና ፈርዲናድ ቲ. ደይ ኢለመንተሪ ትምህርት ቤት** (ኖርዝ ቢርገርድ መንገድ፣ በኖርዝ ሃይቪው ሌን እና በሪዲንግ ጎዳና መካከል)
- **ጆርጅ ዋሺንግተን ሚድል ትምህርት ቤት** (ማውንት ቬርኖን ጎዳና፣ በብራዶክ መንገድ እና በሉራይ ጎዳና መካከል)




ከተማው ከላይ የተገለጹትን ቦታዎች የመረጠው የመኪና ግጭት ታሪክ፣ የትራፊክ መጠን፣ የተሽከርካሪዎች ፍጥነት እና የተማሪዎች እድሜና በረዘት የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መረጃ-መር ሂደት በመጠቀም ነው። ካሜራዎቹ በዚህ የጸደይ ወቅት ይተከላሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ በኋላ ፕሮግራሙ ወደ ሙከራ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ይሸጋገራል። ፕሮግራሙ ለ 2023-24 የትምህርት ዘመን እንዲሰራ (አክቲቭ) ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል።

እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ዞን በርዝመቱ ወደ ¼ ማይል ሲሆን የትምህርት ቤት ምልክቶች በሚያንጸባርቁበት ጊዜ ማለትም የፍጥነት ካሜራዎቹ ስራ ላይ ሲሆኑ 15 MPH የፍጥነት ገደብ አላቸው። ለአሽከርካሪዎች ወደ ፍጥነት ካሜራ ዞን እየገቡ መሆናቸውን ለማሳወቅ ግልጽ የሆኑ ምልክቶች እንዲታዩ ይደረጋሉ።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ ምክር ቤት ጥቅምት 2022 ውስጥ በትምህርት ቤት እና በስራ ዞኖች ውስጥ የፍጥነት ካሜራዎች መጠቀምን የሚፈቅድ ደንብ ያጸደቀ ሲሆን አምስት የፍጥነት ካሜራዎችን ፈንድ ማድረግ በ 2023 የበጀት ዓመት የጸደቀ በጀት ውስጥ ተካቷል።

ከተማው ደህንነታቸው የተጠበቁ መንገዶችን ለትምህርት ቤት ለማቅረብ ተግቶ የሚሰራ ሲሆን ወላጆች እና አሳዳጊዎች ልጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት በእግራቸው ወይ በብስክሌት ስለሚሄዱበት ሁኔታ ሲጠየቁ ከጠቀሷቸው ዋና ዋና ስጋቶች መካከል አንዱ የተሽከርካሪ ፍጥነት ነው። የፍጥነት ካሜራዎች በዩኤስ ትራንስፖርት መምሪያ መሰረት (USDOT) የተሽከርካሪዎችን የግጭት ብዛት ከ 50 በመቶ በላይ መቀነስ የሚችሉ አስተማማኝነታቸው የተረጋገጠ የደህንነት ማስከበርያ መሳርያዎች ናቸው። በተጨማሪም ፖሊስ መኮንኖች በከተማው ውስጥ ያሉባቸውን ሌሎች ስራዎቻቸውን እንዲሰሩ ነጻ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

የፍጥነት ካሜራዎቹ የራዳር ቴክኖሎጂን በመጠቀም የፍጠነት ገደብ ጥሰቶችን ወድያውኑ መዝግበው ይይዛሉ። ቃለ መሀላ የፈጸመ ህግ አስከባሪ መኮንን ጥሰቱ መፈጸሙን ካረጋገጠ በኋላ፣ የተጠቀሰው የፍጥነት ገደብ ጥሰት ለተሽከርካሪው ባለቤት፣ ተከራይ ወይም አከራይ በፖስታ ይላካል። ከፍተኛው የገንዘብ ቅጣት መጠን $100 ነው።

**ስለከተማው የፍጥነት ካሜራ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት alexandriava.gov/go/3785 የሚለውን ድረገጽ ይጎብኙ።**

ከዜና ዘጋቢ ብዙሃን መገናኛ ብቻ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች፣ በዚህ አድራሻ newsroom@alexandriava.gov ወይም በስልክ ቁጥር 703.746.3969 በመደወል ከመገናኛ እና የህዝብ መረጃ ጽ/ቤት ጋር ይገናኙ።

# # #

ይህ ጋዜጣዊ መግለጫ በ alexandriava.gov/go/4476 ላይ ይገኛል።